መልእክት አሥራ አንድ

## በጉ-አምላክ በከተማይቱ ውስጥ በዙፋን ላይ መሆኑ

የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ፦ ራእ. 4፥2-3፤ 22፥1-5፤ 21፥23፤ ሕዝ. 1፥22፣ 26-28

### I. በጉ-አምላክ በከተማይቱ ውስጥ በዙፋን ላይ ነው—ራእ. 4፥2-3፤ 22፥1-5፤ 21፥23፦

ሀ. *የእግዚአብሔርና የበጉ ዙፋን* እግዚአብሔር እና በጉ አንድ መሆናቸውን—በጉን-አምላክ፣ የሚቤዠውን አምላክ—በማመልከት ለእግዚአብሔርም ለበጉም አንድ ዙፋን እንዳለ ያሳያል—22፥1፤ 4፥2-3።

ለ. በዘላለም ውስጥ በዙፋኑ ላይ የሚቀመጠው አምላክ ለአቅርቦታችንና ለእርካታችን ከዙፋኑ የሕይወት ውኃ ወንዝ የሚወጣበት የሚቤዠው አምላካችን ነው።

ሐ. ይህ የሚያሳየው ሦስታንዱ አምላክ—እግዚአብሔር፣ በጉ እና በሕይወት ውኃ በምልክት የታየው መንፈስ—በራስነቱ ሥር (በዙፋኑ ሥልጣን እንደተመለከተው) ለዘላለም ራሱን ወደተዋጁት ሕዝቡ ውስጥ እንደሚያድል ነው።

### II. ዙፋኑ የክርስትና ሕይወታችን ማዕከል ነው፦

ሀ. በየዕለት ሕይወታችን፣ በቤተሰብ ሕይወታችን፣ በትዳር ሕይወታችን፣ በሥራ ሕይወታችን እና በቤተ ክርስቲያን ሕይወታችን ማዕከሉ የእግዚአብሔር ዙፋን መሆን አለበት፤ ሁሉም ነገር ለራስነቱ መገዛት አለበት።

ለ. በየማለዳው ከተነሣን በኋላ፣ "ጌታ ሆይ፣ አንተን እንደ ጌታዬ ስለ ምወስድበት አዲስ ቀን ተመስገን። ቀኑን ሙሉ ራሴን ከራስነትህ ሥር አስገዛለሁ። ጌታ ሆይ፣ በሕይወቴ ውስጥ ዙፋንህን መሥርት። በማንነቴ ማዕከል ላይ ዘፋንህን መሥርት። ጌታ ሆይ፣ መላው ቀኔን ከዕለት ሕይወቴ ጋር ወደ ዙፋንህ ሥር አምጣው" ማለት ያስፈልገናል፤ በየማለዳው እንዲህ ያለውን ጸሎት ለሦስታንዱ አምላክ የምናቀርብ ከሆነ፣ ከዚያ ጊዜ አንሥቶ የሕያው ውኃ ፍሰት በውስጣችን ይኖረናል።

ሐ. በልምምዳችን፣ ሦስታንዱን አምላክ እንደ ራሳችን በመውሰድ ራሳችንን ለእርሱ በምናስገዛበት ጊዜ ሁሉ፣ በውስጣችን ፍሰቱን እንደሰታለን፤ ወንዙ፣ ካቀደው እግዚአብሔር፣ ከተቤዠው በጉ እና አሁን ሁሉን-ያካተተ፣ በሂደት ያለፈ፣ ሕይወትን የሚሰጥ መንፈስ ከሆነው መንፈስ ጋር ይፈሳል።

መ. ከራስነቱ ሥር የሕይወትን ፍሰት ከሕይወት አቅርቦትና ከሕይወት መንገድ ጋር እንደሰታለን፤ በሕይወት ፍሰት ውስጥ እናገለግለዋለን፣ እናየዋለን ከእርሱም ጋር እንነግሣለን—22፥2-5።

### III. በመንፈሳዊ ልምምዳችን ከፍተኛው ነጥብ የእግዚአብሔር ዙፋን ከላዩ ያለው የጠራ ሰማይ ያለው ሰው መሆን እንደሆነ ሕዝቅኤል 1 ይገልጣል፤ እዚህ ነጥብ ላይ መድረስ ማለት በሁሉም ነገር እግዚአብሔር ፊተኛው ስፍራ እንዲኖረው እንፈቅዳለን፣ ለሥልጣኑ እና ለአስተዳደሩም ሙሉ ለሙሉ የምንገዛ ነን ማለት ነው—ቁ. 22፣ 26፦

ሀ. ከሕያዋኑ ፍጡሮቹ ራስ በላይ ያለው መንፈሳዊ ሰማይ በረዶ የሚመስል የጠፈር አምሳያ ያለው ሆኖ እንደመስታወት የጠራ ነው፤ በተጨማሪም፣ ይህ ሰማይ የተዘረጋ እና እንደ መስታወት የረጋ እና የማይለዋወጥ ነው—ቁ. 22።

ለ. እንዲህ ባለ ሁኔታ፣ በእኛና በእግዚአብሔር መካከል ምንም የለም፣ በእኛና እርስ በርሳችን መካከል ምንም የለም፤ ከጌታ ጋር እና እርስ በርሳችን ጥልቅ ዝርዝር እና ግልጽ ኅብረት አለን።

ሐ. ይህ በእግዚአብሔር እና በሰዎች ፊት በደል የሌለው ንጹህ ሕሊናን መጠበቅ ይጠይቃል—ሐዋ. 24፥16።

መ. ዙፋኑ የክርስቶስ የሚገዛ መገኘት ነው፦

1. የጌታ መገኘት ሁልጊዜም ከዙፋኑ ጋር ነው፤ የጌታ ዙፋን በሦስተኛው ሰማይም በመንፈሳችንም ውስጥ ነው—ራእ. 4፥2-3፤ ዕብ. 4፥16፤ ተዛ. 2 ጢሞ. 4፥22፦
    - ሀ. በሰማይ በዙፋኑ ላይ የተቀመጠው ክርስቶስ (ሮሜ 8፥34) አሁን በውስጣችን (ቁ. 10)፣ ማለትም፣ የእግዚአብሔር መኖሪያ ባለበት በመንፈሳችንም ውስጥ ነው (2 ጢሞ. 4፥22)።
    - ለ. የሰማይ ደጅ በሆነችው ቤቴል፣ በእግዚአብሔር ቤት፣ በእግዚአብሔር መኖሪያ ስፍራ፣ ክርስቶስ ምድርን ከሰማይ የሚያገናኝና ሰማይን ወደ ምድር የሚያመጣ መሰላል ነው—ዘፍ. 28፥12-17፣ ዮሐ. 1፥51።
    - ሐ. ዛሬ መንፈሳችን የእግዚአብሔር መኖሪያ ስፍራ ስለሆነ፣ ክርስቶስ እኛን በምድር ያለነውን ሕዝብ ከሰማይ የሚያገናኝበት እና ሰማይን ወደ እኛ የሚያመጣበት መሰላል የሆነበት የሰማይ ደጅ ነው።

መ. ስለዚህ፣ ወደ መንፈሳችን በምንዞር ጊዜ ሁሉ፣ በሰማይ ደጅ በኩል በመግባት በክርስቶስ እንደ ሰማያዊው መሰላል በሰማይ ያለውን የጸጋ ዙፋን እንነካለን።

2. እንደ በረዶ ከጠራው ጠፈር በላይ ያለው ዙፋን፣ በክርስትና ሕይወታችንና በቤተ ክርስቲያን ሕይወታችን የጠራ ሰማይ በሚኖረን ጊዜ ሁሉ፣ በዙፋኑ አገዛዝ ሥር እንደምንሆን ያመለክታል፤ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያለው ሥልጣን ከጠራው ሰማይ በላይ ያለው ዙፋን ነው።

3. ዙፋኑ እግዚአብሔር በእኛ ላይ እንዲገዛ ብቻ ሳይሆን እግዚአብሔር ዘላለማዊ አላማውን እንዲፈጽምም ነው፤ በመንፈሳዊ ሕይወታችን ዙፋኑ ካለን፣ እግዚአብሔር በእኛ ላይ መግዛት ብቻ ሳይሆን በእኛ ውስጥ፣ ከእኛ ጋር እና በእኛ በኩል አላማውን ይፈጽማል—ሮሜ 5፥17፣ 21፤ ተዛ. ማቴ. 28፥18-20።

4. ዙፋኑ የሰንፔር ድንጋይ መልክ አለው፤ ቀለሙ ሰማያዊ የሆነው የሰንፔር ድንጋይ የክርስቶስን የሚገዛ መገኘት ሰማያዊ ውጫዊ ሁኔታ፣ ውስጣዊ ሁኔታ እና ከበብ ያመለክታል—ዘጸ. 24፥10።

**IV. ሕዝቅኤል 1 በዙፋኑ ላይ ያለው ሰውን እንደሚመስል ይገልጣል፣ ሆኖም በዙፋኑ ላይ የተቀመጠው አምላክም ሰውም እንደሆነ በማመልከት የያሕዌ ክብር መልክ አለው፤ ይህ አምላክ-ሰው የሆነው፣ የአምላክ እና የሰው መዋሐድ የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ ነው—26፣ 28፦**

ሀ. ኢየሱስ ክርስቶስ ሙሉ አምላክ ነበር፣ ሰው ለመሆንም ሥጋ ለብሷል፤ የሰው ባሕርይ ይዞ እንደ ሰው ኖረ፣ ሞተ፣ ከሞት ተነሣና ዐረገ፤ አሁን በዙፋኑ ላይ እንዳለው ማንነት፣ አሁንም ድረስ የሰው ልጅ ነው—ዮሐ. 1፥1፣ 14፤ 6፥62፤ ሐዋ. 7፥56፣ 59-60።

ለ. ስለዚህ፣ ከጌታ ኢየሱስ ዕርገት ጀምሮ ሰው በዙፋን ላይ ነበር፤ በሺው ዓመት እና በአዲሱ ሰማይ እና በአዲሱ ምድር ለዘላለም፣ ሰው በዙፋኑ ላይ ይኖራል—ማቴ. 19፥28፤ ራእ. 22፥1፣ 3።

ሐ. ከሰው ጋር ባለው ግንኙነት የእግዚአብሔር ምሥጢራዊ ውጥን ራሱን ከሰው ጋር ማዋሐድ እና በዚያም ከሰው ጋር አንድ ዓይነት መሆን እና ሰውን በሕይወት፣ በባሕርይ እና በመገለጥ ተመላኪነቱን ግን ሳይጨምር ከራሱ ጋር አንድ ዓይነት ማድረግ ነው፤ ሰው በእግዚአብሔር መልክ የተፈጠረው እግዚአብሔርን ለመግለጥ እና ለእግዚአብሔር ለመግዛት ነበር—ዘፍ. 1፥26-28፤ ተዛ. ኢሳ. 14፥12-14፦

1. በምድር ያሉት አራቱ ሕያዋን ፍጡራን በዙፋኑ ላይ ያለው የእርሱ መገለጥ መሆናቸውን በማመልከት በዙፋኑ ላይ ያለው እና አራቱ ሕያዋን ፍጡራን ሁለቱም የሰው መልክ አላቸው፤ ይህ መገለጥ የእግዚአብሔር በስብዕና መገለጥ ነው—ሕዝ. 1፥5፤ 1 ጢሞ. 3፥15-16።

2. በሰማይ ያለው እግዚአብሔር ለመገለጡ ወደ ሰው ውስጥ ራሱን በመሥራት በምድር ያለውን ሰው ማግኘት ይፈልጋል፤ በተጨማሪም፣ የእግዚአብሔር ውጥን ሰው በዙፋኑ ላይ ይሆን ዘንድ በሰው ላይ መሥራት ነው—ኤፌ. 3፥16-21፤ ራእ. 3፥21፤ 5፥10፤ 20፥4፤ 22፥5፤ ማቴ. 19፥28።

3. ጌታ ኢየሱስ እንደ ቀዳሚው፣ እንደ ፊር ቀዳጁ፣ ወደ ክብር ለመግባት መንገዱን ቀዶ በዙፋኑ ላይ ተቀምጧል፣ እኛም ብዙ ወንድሞቹ አሁን እየተከተልነው ነው—ዕብ. 2፥6-12፤ ራእ. 3፥21፤ 22፥5።

**V. ሕዝቅኤል 1 በዙፋኑ ላይ የተቀመጠው ሰው መልክ ሁለት ገጽታዎች እንዳሉት ይናገራል፦ ከወገቡ በላይ በእሳት መካከል እንዳለ የጋለ ብረት አምሳያ ነበረው፤ ከወገቡ በታች ደግሞ የእሳት አምሳያ ነበረው—27፦**

ሀ. በእሳት መካከል እንዳለ የጋለው ብረት የወርቅ እና የብር ደብልቅ የሆነ የሚያበራ ብረት ነው፤ ወርቅ የእግዚአብሔርን ባሕርይ ያመለክታል፤ ብር ደግሞ ቤዛነትን ያመለክታል፤ ስለዚህ፣ ከወርቅ እና ከብር የተዋቀረው በእሳት መካከል እንዳለ የጋለው ብረት ፣ በጉን-አምላክ፣ የሚቤዠውን አምላክ ያመለክታል—ቁ. 4።

ለ. ከወገቡ እስከ ራሱ ያለው የሰው የላይኛው ክፍል ባሕርይውን እና ጸባዩን በመወከል የስሜት ክፍል ነው፤ በዙፋኑ ላይ ያለው ጌታ ኢየሱስ በባሕርይው እና በጸባዩ መሠረት የሚቤዠውን አምላክ በማመልከት በእሳት መካከል እንዳለ የጋለ ብረት መልክ አለው።

ሐ. የሰው የታችኛው ክፍል ለእንቅስቃሴ ነው፤ ከወገብ በታች ያለው የእሳት አምሳያ በእግዚአብሔር በሚነድና በሚቀድስ ኃይል በሆነው በእንቅስቃሴው ውስጥ ያለውን የጌታን መልክ ያመለክታል።

መ. ጌታ ወደ እኛ ሲመጣ፣ አብርሆት ለመስጠት፣ ለመመርመር እና ለማንደድ እንደ እሳት ይመጣል፤ ከዚያም በእሳቱ በኩል፣ የሚያበራው በእሳት መካከል እንዳለ የጋለው ብረት ይሆንልናል፣ እኛም በሚቤዠው አምላክ የሚያንጸባርቅ መገለጥ እንሞላለን።

ረ. የሚባላ እሳት በሆነው ጌታ (ዕብ. 12፥29) አሉታዊዎቹ ነገሮች ሁሉ ከእኛ ላይ ተቃጥለው ከተወገዱ በኋላ፣ በእኛ ውስጥ የሚቀረው በእሳት መካከል እንዳለ የጋለው ብረት፣ የሚቤዡው አምላክ ነው።

VI. **ሕዝቅኤል 1 በዙፋኑ ላይ ባለው ጌታ ዙሪያ ያለውን ግርማ እና ክብር በማመልከት በዙፋኑ ላይ በተቀመጠው ሰው ዙሪያ እንደ ፀዳል አምሳያ ቀስተደመና እንዳለ ይናገራል—ቁ. 28፤ ራእ. 4፥3፦**

ሀ. በኖኅ ጊዜ በደመና ውስጥ የነበረው ቀስተደመና እግዚአብሔር በድጋሚ የሰውን ዘር በጎርፍ ፈጽሞ እንደማያጠፋ በማመልከት ከሰው እና ከሁሉም ሕያዋን ፍጥረታት ጋር ያለውን ቃልኪዳን በመጠበቅ የእግዚአብሔር ታማኝነት ምልክት ነበር—ዘፍ. 9፥13።

ለ. ቀስተ ደመና ከሦስት መሠረታዊ ቀለሞች እንደተዘጋጀ መቁጠር ይቻላል—ቀይ፣ ቢጫ እና ሰማያዊ፦ ቀይ፣ የእሳት ቀለም፣ የእግዚአብሔርን ቅድስና ያመለክታል፤ ቢጫ፣ በእሳት መካከል እንዳለ የጋለ ብረት ቀለም፣ የእግዚአብሔርን ክብር ያመለክታል፤ ሰማያዊ፣ የሰንፔር ዙፋን ቀለም፣ የእግዚአብሔርን ጽድቅ ያመለክታል—መዝ. 89፥14፦

1. የእግዚአብሔር ጽድቅ፣ ቅድስና እና ክብር ኃጢአተኞችን ከእግዚአብሔር የሚያርቁ ሦስት መለኮታዊ ባሕርያት ናቸው—ዘፍ. 3፥24።
2. ሆኖም፣ ክርስቶስ መጣ፣ የእግዚአብሔርን የጽድቅ፣ የቅድስና እና የክብር ጥያቄዎች ለማርካት በመስቀል ላይ ሞተ፣ ከሞትም ተነሣ፣ አሁን እርሱ ጽድቃችን፣ ቅድስናችን እና ክብራችን ነው—1 ቆሮ. 1፥30።
3. አሁን፣ እኛ አማኞች በክርስቶስ ውስጥ ስለሆንን፣ በእግዚአብሔር ፊት እንደ ጽድቅ፣ ቅድስና እና ክብር የክርስቶስ መልክ አለን፤ ይህ የወደቅነውን እኛን በኃጢአተኞች ላይ ካለው ፍርዱ በማዳኑ እንደ የእግዚአብሔር ታማኝነት ምስክር የቀስተደመና መልክ ነው።
4. መሠረቶቿ የቀስተደመና መልክ ያላቸው ከተማ በሆነችው በአዲሲቱ ኢየሩሳሌም (ራእ. 21፥19-20)፣ የዳኑ አማኞች ጥቅል ድምር የሆንን እኛ የእግዚአብሔርን ጽድቅ፣ ቅድስና እና ክብር ጸዳል የምናንጸባርቅና እግዚአብሔር ጻድቅ እና ታማኝ እንደሆነ ለዘላለም የምንመሰክር ቀስተደመና እንሆናለን።
5. በሕዝቅኤል 1 በስእል እንደተገለጠው፣ የክርስትና ሕይወት እና የቤተ ክርስቲያን ሕይወት እንዲህ ባለ ቀስተደመና ይጠናቀቃል፤ በዚያ ጊዜ የእግዚአብሔር ዘላለማዊ እቅድ ይጠናቀቃል።

*© 2025 Living Stream Ministry*